የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ

# FEDERAL NEGARIT GAZETTE

## OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

ሃያኛ ዓመት ቁጥር ፴፰
አዲስ አበባ ግንቦት ፳፩ ቀን ፪ሺ፮ ዓ.ም

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

20th Year No. 38
ADDIS ABABA 29th May, 2014


ማውጫ


አዋጅ ቁጥር ፰፻፴፭ /፪ሺ፮ ዓ.ም

ለሦስተኛው የአርብቶ አደር አካባቢዎች ልማት ፕሮጀክት ማስፈፀሚያ የሚውል ብድር ከዓለም አቀፍ የልማት ማህበር ለማግኘት የተፈረመው የብድር ስምምነት ማፅደቂያ አዋጅ........................................................ገጽ ፯ሺ፬፻


CONTENTS


Proclamation No. 835/2014

International Development Association Financing Agreement for the Pastoral Community Development Project III Ratification Proclamation............Page 7400


## አዋጅ ቁጥር ፰፻፴፭/፪ሺ፮

## በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግስት እና በዓለም ዓቀፍ የልማት ማህበር መካከል የተደረገውን የብድር ስምምነት ለማፅደቅ የወጣ አዋጅ

ለሦስተኛው የአርብቶ አደር አካባቢዎች ልማት ፕሮጀክት ማስፈፀሚያ የሚውል ፸፩ ሚሊዮን ፰፻ሺ. ኤስ.ዲ.አር (ሰባ አንድ ሚሊዮን ስምንት መቶ ሺ. ኤስ.ዲ.አር) የሚያስገኘው የብድር ስምምነት በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግስት እና በዓለም ዓቀፍ የልማት ማህበር መካከል እ.አ.አ ጃንዋሪ ፲፮ ቀን ፪ሺ፲፬ በአዲስ አበባ የተፈረመ በመሆኑ፤

ይህንኑ የብድር ስምምነት የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት መጋቢት ፳፭ ቀን ፪ሺ፮ ዓ.ም ባካሄደው ስብሰባ ያፀደቀው በመሆኑ፤

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግሥት አንቀጽ ፶፭(፩) እና (፲፪) መሠረት የሚከተለው ታውጇል።

## PROCLAMATION No. 835/ 2014

## A PROCLAMATION TO RATIFY THE FINANCING AGREEMENT BETWEEN THE GOVERNMENT OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA AND THE INTERNATIONAL DEVELOPMENT ASSOCIATION

WHEREAS, a Financing Agreement, between the Government of the Federal Democratic Republic of Ethiopia and the International Development Association stipulating that the Internatinal Development Association provide to the Federal Democratic Republic of Ethiopia a credit amount of 71,800,000 SDR (seventy one million eight hundred thousand Special Drawing Rights) for financing Pastoral Community Development Project III was signed in Addis Ababa on the 16th day of January, 2014;

WHEREAS, the House of Peoples' Representatives of the Federal Democratic Republic of Ethiopia has ratified said Financing Agreement at its session held on the 3rd day of April, 2014;

NOW, THEREFORE, in accordance with Article 55 (1) and (12) of the Constitution of the Federal Republic of Ethiopia, it is hereby proclamined as follows:

**፩ አጭር ርዕስ**

ይህ አዋጅ "ለሦስተኛው የአርብቶ አደር አካባቢዎች ልማት ፕሮጀክት ማስፈፀሚያ የሚውል ብድር ከዓለም ዓቀፍ የልማት ማህበር ለማግኘት የተፈረመው የብድር ስምምነት ማፅደቂያ አዋጅ ቁጥር ፰፻፴፭/፪ሺ፮" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

**፪ የስምምነቱ መፅደቅ**

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግስት እና በዓለም ዓቀፍ የልማት ማህበር መካከል እ.አ.አ ጃንዋሪ ፲፮ ቀን ፪ሺ፲፬ በአዲስ አበባ የተፈረመው የብድር ስምምነት ቁጥር 5335- ET በዚህ አዋጅ ፀድቋል።

**፫ የገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር ሥልጣን**

የገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር በብድር ስምምነቱ የተገኘውን ፸፩ ሚሊዮን ፰፻ሺ ኤስ.ዲ.አር (ሰባ አንድ ሚሊዮን ስምንት መቶ ሺ ኤስ.ዲ.አር) በብድር ስምምነቱ በተመለከቱት ሁኔታዎች መሠረት በሥራ ላይ እንዲውል ለማድረግ በዚህ አዋጅ ሥልጣን ተሰጥቶታል።

**፬ አዋጁ የሚፀናበት ጊዜ**

ይህ አዋጅ በፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል።

አዲስ አበባ ግንቦት ፳፱ ቀን ፪ሺ፮ ዓ.ም

ዶ/ር ሙላቱ ተሾመ
የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
ፕሬዚዳንት

**1. Short Title**

This Proclamation may be cited as the "International Development Association Financing Agreement for the Pastoral Community Development Project III Ratification Proclamation No. 835/2014".

**2. Ratification of the Agreement**

This Financing Agreement Credit Number 5335-ET signed in Addis Ababa on the 16th day of January 2014 between the Government of the Federal Democratic Republic of Ethiopia and the International Development Association is hereby ratified.

**3. Power of the Ministry of Finance and Economic Development**

The Ministry of Finance and Economic Development is hereby empowered to undertake all acts necessary for the utilization of the credit amount of 71,800,000 SDR (seventy one million eight hundred thousand Special Drawing Rights) in accordance with the terms and conditions set forth in the Financing Agreement.

**4. Effective Date**

This Proclamation shall enter into force on the date of publication in the Federal Negarit Gazette.

**Done at Addis Ababa, this 29th day of May, 2014.**

**MULATU TESHOME( DR.)**

**PRESIDENT OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA**